# አውቶማቲክ የገንዘብ መክፈያ ማሺን

አውቶማቲክ የገንዘብ መክፈያ ማሺን (ኤቲኤም) የኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ወይም የሌሎች ባንኮችን ካርዶች በመጠቀም ከባንክ ሒሳብ ገንዘብ ማውጣት እና ሂሳብ ማንቀሳቀስ፣ እንዲሁም የተለያዩ ተጨማሪ አገልግሎቶችን ማግኘት የሚያስችል ዘመናዊ መሣሪያ ነው።

1. **የኤቲኤም ጥቅም**

- ያለ ባለሙያ እርዳታ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፤
- በማንኛውም ጊዜ (24/7) አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፤
- ጊዜዎን ይቆጥባሉ፤
- ጥሬ ገንዘብ በመያዝ ለዝርፊያና ለመሳሰሉት አደጋዎች ከመጋለጥ ይድናሉ፡፡

2. **የኤቲኤም አገልግሎቶች**

- ጥሬ ገንዘብ ማውጣት፤
- ገንዘብ ከአንድ የግል ሂሳብ ወደ ሌላ የግል ሂሳብ ወይም በባንኩ ሂሳብ ላለው ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ፤
- ቀሪ ሂሳብ ማወቅ።

3. **የምንዛሪ አገልግሎት**

ከላይ ከተጠቀሱት አገልግሎቶች በተጨማሪ በተወሰኑ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አውቶማቲክ የውጭ ገንዘብ መክፈያ ማሺኖች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ምንዛሪ አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡፡

3.1. **ምንዛሪ የሚሰጥባቸው ገንዘቦች**

- የአሜሪካን ዶላር
- ዩሮ
- የእንግሊዝ ፓውንድ

### 3.2. የምንዛሪ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን የሚችለው ማነው?

- ከላይ የተጠቀሱት የውጭ ሀገር ገንዘቦች ያለው ማንኛውም ግለሰብ በአገልግሎቱ ተጠቃሚ መሆን ይችላል።
- የውጪ ምንዛሪ አገልግሎት ተጠቃሚ ለመሆን የባንኩ ደንበኛ መሆን ወይም የባንክ ካርድ መያዝ አያስፈልግም::

## 4. የኤቲኤም አጠቃቀም

- ማሺኑ ላይ ብርት ጥፍት በማለት ምልክት የሚሰጠው ማስገቢያ ውስጥ ካርዱን የቀስት ምልክት ባለበት በኩል በማስቀደም ያስገቡ፤
- "Please enter your PIN" "እባክዎን የሚስጥር ቁጥሩን ያስገቡ" የሚለው ጽሑፍ ሲመጣ የምስጢር ቁጥርዎን በጥንቃቄ በመጫን ያስገቡ፤
- ማሺኑ ካርድዎ የያዘውን መረጃ ትክክለኛነት እስኪያረጋግጥ "Please wait" "እባክዎ ትንሽ ይጠብቁ" የሚል ጽሑፍ ያሳያል፤
- ማሺኑ ተገቢውን የማረጋገጥ ሥራ ካከናወነ በኋላ የሚከተሉትን የአገልግሎት አማራጮች ያሳያል።

| | |
|---|---|
| Mini Statement<br>የአጭር ጊዜ የሂሳብ ማመሳከሪያ | Withdrawal<br>ወጪ |
| Transfer<br>ወደ ሂሳብ ማዛወሪያ | Balance<br>ቀሪ ሂሳብ |
| | PIN Change<br>የሚስጥር ቁልፍ መለወጫ |

### 4.1. የገንዘብ እንቅስቃሴ ማከናወን

#### 4.1.1. ገንዘብ ወጪ ማድረግ

- ገንዘብ ወጪ ለማድረግ "Withdrawal" "ወጪ" የሚለውን አማራጭ ሲጫኑ ማሺኑ እስከ ብር 4,000 ያስመርጥዎታል:: የሚፈልጉትን የገንዘብ መጠን የያዘውን አማራጭ ይጫኑ፡፡ ሆኖም የተዘረዘሩት የገንዘብ አማራጮች ከእርስዎ ፍላጎት ውጭ ከሆኑ "Other Amount" "ሌላ መጠን" የሚለውን

አማራጭ በመጫን የፈለጉትን የገንዘብ መጠን ፅፈው ማስገባት ይችላሉ። በዚህ ጊዜ ደረሰኝ መፈለግዎን የሚጠይቅ “Do you want receipt?” የሚል አማራጭ የሚሰጥዎ ሲሆን፤ ከፈለጉ “Yes” ከሚለው ጎን፣ ካልፈለጉ ግን “No” ከሚለው ጎን ያለውን ምልክት ይጫኑ።

- ማሺኑ ሥራውን ካከናወነ በኋላ:-
  - ካርድዎን በመመለስ እንዲወስዱ ይጠብቅዎታል፤
  - ካርድዎን ከወሰዱ በኋላ ገንዘብዎን ከገንዘብ ማውጫ ቀዳዳው በፍጥነት ይውሰዱ፤
  - ደረሰኙንም ከደረሰኝ ማውጫ ቀዳዳ ጠብቀው ይውሰዱ፡፡

**ማስታወሻ**:- ማሺኑ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ካሰማ በኋላ ካርድዎን ካልወሰዱ ካርዱን ወደ ውስጥ መልሶ ካርድ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ያስቀምጠዋል፤ካርድዎን በተገቢው ጊዜ ስላልወሰዱም ገንዘብዎን አያገኙም፡፡

### 4.1.2. ገንዘብ ማስተላለፍ

ገንዘብ ከአንድ ሂሳብ ወደ ሌላ ወይም ወደ ሦስተኛ ወገን ለማስተላለፍ “Transfer” “ወደ ሂሳብ ማዛወሪያ” የሚለውን አማራጭ ሲጫኑ የባንክ ሂሳብዎ ከአንድ በላይ ከሆነ ገንዘብ ተቀናሽ የሚደረግበትን ሂሳብ እንዲመርጡ ይጠይቅዎታል። የባንክ ሂሳብዎ አንድ ብቻ ከሆነ ግን ገንዘብ የሚያስተላለፉለትን ሂሳብ ቁጥር እንዲያስገቡ ይጠየቃሉ። ከዚያም የገንዘቡን መጠን በማስገባትና በመተየቢያው ላይ ያለውን አረንጓዴ ቁልፍ (Enter) በመጫን ያረጋግጡ፡፡

ከዚህ በኋላ ማሺኑ ካርድዎን በመመለስ እንዲወስዱ ይጠብቅዎታል፡፡ ካርድዎን ከወሰዱ በኋላ ደረሰኙንም ከደረሰኝ ማውጫው ቀዳዳ ጠብቀው ይውሰዱ፡፡ ማሺኑ የማስጠንቀቂያ ድምፅ ካሰማ በኋላ ካርድዎን ካልወሰዱ ግን ካርዱን ወደ ውስጥ በመመለስ ካርድ ማስቀመጫ ክፍል ውስጥ ያኖረዋል ::

### 4.1.3. ቀሪ ሂሳብን ማወቅ

- “Balance” “ቀሪ ሂሳብ” የሚለውን አማራጭ ሲጫኑ፣ በሂሳብዎ ውስጥ የቀረው የገንዘብ መጠን ስክሪኑ ላይ ስለሚፃፍ ከዚያ ላይ ማንበብ ይችላሉ፡፡

5. **በአንድ ቀን ምን ያህል ገንዘብ ወጪ ማድረግ ወይም ወደ ሌላ ሂሳብ ማዘዋወር ይቻላል ?**

የገንዘቡ ብዛት በሚገለገሉበት የካርድ አይነት የሚወሰን ሆኖ በአንድ ቀን በኤቲኤም

| **ተ.ቁ** | **የካርዱ አይነት** | **ወጪ ሊደረግ የሚችለው የገንዘብ መጠን** | **ወደ ሌላ ሂሳብ ሊተላለፍ የሚችለው የገንዘብ መጠን** |
|---|---|---|---|
| 1 | የስጦታ ካርድ (ዋሌት ካርድ) | በካርዱ ላይ ያለውን ገንዘብ ያህል | |
| 2 | ቪዛ ክላሲክ ዴቢት ካርድ | እስከ ብር 10,000 | እስከ ብር 100,000 |
| 3 | ቪዛ ክላሲክ የሴቶች ዴቢት ካርድ | እስከ ብር 10,000 | እስከ ብር 100,000 |
| 4 | ቪዛ ክላሲክ ሰላም ካርድ | እስከ ብር 10,000 | እስከ ብር 100,000 |
| 5 | ቪዛ ጎልድ ዴቢት ካርድ | እስከ ብር 15,000 | እስከ ብር 150,000 |
| 6 | ቪዛ ፕላቲንየም ዴቢት ካርድ | እስከ ብር 20,000 | እስከ ብር 200,000 |
| 7 | ኮ ብራንድድ ቪዛ ፕላቲንየም ዴቢት ካርድ | እስከ ብር 20,000 | እስከ ብር 200,000 |

አማካኝነት ወጪ ሊደረግ ወይም ወደ ሌላ ሂሳብ ሊዛወር የሚችለው ገንዘብ ከታች በሚገኘው ሰንጠረዥ ተመልክቷል።

6. **የምስጢር ቁጥር ቢረሳ ወይም በሌላ ሰው ቢታወቅ ምን ማድረግ ይቻላል?**

የምስጢር ቁጥርዎን ከረሱ ወይም በሌላ ሰው ከታወቀ የሚከተለውን ይፈጽሙ፡፡

- በመጀመሪያ ካርዱን ወደወሰዱበት የባንኩ ቅርንጫፍ በመሄድ ጉዳዩን ያሳውቁ፣
- የሚሰጥዎትን የምስጢር ቁጥር መቀየሪያ ቅጽ ይሙሉ፣
- አዲስ የሚስጥር ቁጥር ይሰጥዎታል፡፡

7. **ካርድዎ ቢጠፋ / ቢሰረቅ ምን ማድረግ ያስፈልጋል?**

የተሰጠዎት የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ካርድ ቢጠፋብዎ ወይም ቢሰረቅብዎ ወዲያውኑ በስልክ ቁጥር 951 ያሳውቁ፡፡ ከዚያም ካርዱን የወሰዱበት ቅርንጫፍ በአካል በመቅረብ የሚሰጥዎትን ቅጽ በመሙላት የሚሰጥዎትን መመሪያ ተግባራዊ ያድርጉ፡፡ በቀድሞው ምትክ አዲስ ካርድ በክፍያ ይሰጥዎታል፡፡

8. **የተሳሳተ የምስጢር ቁጥር መጠቀም**

በተሳሳተ የምስጢር ቁጥር ከሁለት ጊዜ በላይ ለመጠቀም ከሞከሩ ማሺኑ ካርድዎን በመያዝ ካርድዎ ስለመወሰዱ ማስረጃ ይሰጥዎታል፡፡ የተያዘብዎትን ካርድ የት ማግኘት እንደሚችሉ 951 በመደወል ሙሉ መረጃ ማግኘት ይችላሉ።

9. **የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ካርድ ለምን ያህል ጊዜ ያገለግላል?**

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ካርድ የሚያገለግለው ለሶስት ዓመት ብቻ ነው፡፡ ሆኖም ከዚያ በፊት በአያያዝ ጉድለት የተነሳ ቢበላሽ በምትኩ አዲስ ካርድ በክፍያ ማግኘት ይቻላል። የመጀመሪያው ካርድ የሚሰጠው ያለክፍያ ሲሆን፣ የአገልግሎት ጊዜውም ሲያበቃ ማደስ ይቻላል፡፡

10. **የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቅድመ ክፍያ ካርዶች ለምን ያህል ጊዜ ያገለግላሉ?**

በካርዱ የተመዘገበው የገንዘብ መጠን እስካለቀ ድረስ።

11. **በኤቲኤም መጠቀም የአገልግሎት ክፍያ ያስጠይቃል?**

- ገንዘብ ወጪ ለማድረግ በአንድ መቶ ብር አስር ሳንቲም ያስከፍላል፡፡
- ቀሪ ገንዘብ ለማወቅ 0.25 ሣንቲም ያስከፍላል።
- የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ካርድ የያዙ ደንበኞች በሌሎች ባንኮች ኤቲኤም ወጪ ሲያደርጉ 0.50 ሣንቲም ይከፍላሉ።

## 12. የኤቲኤም ተጠቃሚዎች ሊያደርጉት የሚገባ ጥንቃቄ

- የምስጢር ቁጥርን ለማንም ሰው አለመንገር ወይም አለማሳየት፤
- የምሥጢር ቁጥርን የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ካርድ ላይ ወይም ከካርዱ ጋር በቅርብ በሚገኙ ማስታወሻዎች ላይ አለመጻፍ፤
- የምስጢር ቁጥርዎ በሌላ ሰው እንዳይታይ ማሺኑን በተቻለ መጠን በሰውነት ከለል በማድረግ ቁጥሮቹን መጻፍ፤
- ካርዱ እንዳይጠፋ ወይም እንዳይሰረቅ በጥንቃቄ መያዝ ፤
- የተሳሳተ የምስጢር ቁጥር ላለመጠቀም ጥንቃቄ ማድረግ፤
- ስለ ኤቲኤም አጠቃቀም ከሚመለከታቸው የባንኩ ሠራተኞች በስተቀር ከሌላ ሰው ምንም ዓይነት እርዳታ/ምክር አለመጠየቅ፤
- በምንም ዓይነት ሁኔታ ሌላ ሰው ገንዘብ እንዲያወጣልዎ ካርድዎንና የምስጢር ቁጥርዎን አለመስጠት፡፡

## 13. በኤቲኤም ለመጠቀም መሟላት ያለባቸው

- በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፍ ሂሳብ ሊኖርዎት ወይም አዲስ ሂሳብ ሊከፍቱ ይገባል፤
- ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ካርድ የተዘጋጀውን የማመልከቻ ቅጽ በመሙላት ካርድ መያዝ።

## 14. የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የኤቲኤም ማሺኖች የሚገኙባቸው ቦታዎች

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ኤቲኤሞች የሚገኙት፤

- በባንኩ ቅርንጫፎች፣
- በገበያ ማዕከላት፣
- በሆቴሎች፣
- በሆስፒታሎች፣
- በዩኒቨርስቲዎች፣
- በነዳጅ ማደያዎች፣
- በአውሮፕላን ማረፊያ ጣቢያዎች እና በሌሎችም ቦታዎች ነው።